በስመ አብ ወወልድ

ወመንፈስቅዱስ አሐዱ አምላክ

አሜን፡፡

# እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ማን ናት? - ክፍል ሁለት

በቀሲስ ሰሎሞን ሙሉጌታ

ቦሌ ደብረ ሳሌም መድኃኔዓለም ቤተ ክርስቲያን አዳራሽ

ሳምንታዊ መርሐ ግብር - ረቡዕ 12፡30 – 1፡30 ምሽት
የካቲት ፲፰ ቀን ፳፻፩ ዓ.ም.

# እውነተኛኘኙቱ ቤ/ክ በየት ትገኛለች?
# እንዴትስ ትታወቃለች?

- እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን በሐዋርያት የተሰበከውን ንጹሕ የሆነ የክርስትና ትምህርት ጠብቃ የምታስጠብቅና የምታስተምር ናት።

- እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያኒቱ የእግዚአብሔር ልጅ ሰው ሆኖ ወደዚህ ዓለም እንደመጣ ጌታችንም በመስቀል ከመሞቱ አስቀድሞ #እኔ ለእውነት ልመሰክር ስለዚህ ተወልጃለሁ ስለዚህም ወደ ዓለም መጥቻለሁ፤ ከእውነት የሆነ ሁሉ ድምፄን ይሰማል; ዮሐ. 18፡ 37። እንዲሁም ቅዱስ ጳውሎስ ለደቀ መዝሙሩ ለጢሞቴዎስ ሐዋርያዊ ተልእኮውን እንዴት መወጣት እንዳለበት ባስተማረበት ክፍል #ብዘገይ ግን፥ በእግዚአብሔር ማደሪያ ቤት መኖር እንዴት እንደሚገባ ታውቅ ዘንድ እጽፍልሃለሁ፤ ቤቱም የእውነት ዓምድና መሠረት፥ የሕያው እግዚአብሔር ቤተ ክርስቲያን ነው።; 1ኛ ጢሞ 3፡15 እንዳለው ያልተበረዘውን እውነተኛ ትምህርት ለሕዝቡ የምታስተላልፍ ናት።

- ነገር ግን አሁን #በቤተክርስቲያን; ስም የሚጠሩት የአንዳንዶች ገጽታ ከክርስቶስም ሆነ ከሐዋርያት ትምህርት የወጣ መሆኑ የሚያሳዝን ብቻ ሳይሆን የምንቀበለውም ግልጽ ሂደት ነው።

# እውነተኛኘኙቱ ቤ/ክ በየት ትገኛለች?
# እንዴትስ ትታወቃለች?...

- በመጀመሪያ በአቋም ሁሉም እውነትን ሊያስተምሩ እንደማይችሉ መተማመናችን እጅግ አስፈላጊ ነው። ለምሳሌ አንዲቱ ቤተክርስቲያን ቅዱስ ቁርባን እውነተኛው የጌታችን የአምላካችን የመድኃኒታችን የኢየሱስ ክርስቶስ ሥጋና ደም ነው ብላ ስታምንና ስታሳምን ሌላው አይደለም ቢል አንዳቸው ብቻ እንጂ ሁለቱም እውነተኞች ተደርገው በመደዳ አይቆጠሩም።

- ወይም አንዲቱ ቤተክርስቲያን በቅዱስ መስቀል መንፈሳዊ ኃይል ስታምን ሌላው የሚቃወመው ከሆነ አንዳቸው ከእውነት ተሳስተዋል ማለት ነው።

- እውነተኛይቱ ቤተ ክርስቲያን ከጥንታዊቱና ከመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን እምነትና ትምህርት ጋር የማትጣላ ያንን ጠብቃ የምታስጠብቅ ናት።

- አንድ ሰው በትክክል ከዘመኑ ጋር ብቅ ብቅ ያሉትን #አብያተ ክርስቲያናት; ትምህርት ከመጀመሪያይቱ ቤተክርስቲያን አስተምህሮ ጋር በአግባብ ቢያነጻጽር አንዲቱ ኦርቶዶክሳዊት ቤተክርስቲያን ብቻ እውነተኛ፤ ሐዋርያዊትና ጥንታዊቱ ቤተክርስቲያን ሆና ያገኛታል። 2ኛ ተሰሎንቄ 2፡ 15 እና 2ኛ ተሰሎንቄ 3፡ 6

# ***<u>እውነተኛኘኙቱ ቤ/ክ በየት ትገኛለች?</u>***
# ***<u>እንዴትስ ትታወቃለች?...</u>***

- እውነተኛይቱን ቤ/ክ የምናውቅበት ሌላው ምልክት ምዕመናኑን የምታበረታባቸው የእግዚአብሔር ኃይል፤ ስጦታው፤ ረድኤቱና በረከቱ ናቸው።

- ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ የእግዚአብሔር ስጦታ ለምዕመናን በጥምቀት፤ በቅዱስ ቁርባን፤ በክህነት፤ በሜሮን፤ በንስሐ፤ በተክሊል፤ በቀንዲል ይሰጥ ነበር።

- እነዚህን ምስጢራት አስቀድመው የፈጸሙት ሐዋርያት በኋላም ኤጲስ ቆጶሳትና ቀሳውስት ናቸው። ክህነትንም መስጠት በጳጳሳት ይፈጸማል።

- እጅን በመጫን የመሾምም (ክህነት) ሥልጣን ሐዋርያዊ ትውፊት ሲሆን ይኸም ሐዋርያት ጳጳሳትን፤ ቀሳውስትንና ዲያቆናትን በመሾም የጀመሩት ነው።

- ሐዋርያዊ ቅብብል ወይም ትውፊት ሌላውን እንደሚለኩስ የሻማ መብራት ነው። የሻማው እሳት ከጠፋ ሐዋርያዊ ትውፊቱ ተቋረጠ ማለት ነው። ይኸም እውነተኛ መንፈሳዊ መሪ ወይም ትክክለኛው የቤተክርስቲያን ምስጢር አይኖርም ማለት ነው። ውጤቱም የሰውን ልጆች የመዳናቸውን መንገድና ዕድል ማጥፋት ነው።

## እውነተኛኘኘቱ ቤ/ክ በየት ትገኛለች? እንዴትስ ትታወቃለች?...

- ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ ሐዋርያዊ ውርሱ ወይም ቅብብሉ በጥንቃቄ በእምነት ሲጠበቅ የኖረው የመጀመሪያው ሻማ ብርሃን ሳይጠፋ እንዲኖር ነው፡፡ ይኸንን የጠበቁትም ጳጳሳት ውርሱን ለሚገባቸው ጳጳሳት አወረሱ፡፡ በአጠቃላይ እጅን በመጫን (ክህነት) መሾም የተወረሰው ከመጀመሪያዎቹ ሐዋርያት ነው፡፡ በክህደት የተዘፈቁ ወይም ያለአገባብ ይኖሩ የነበሩ #ጳጳሳት; ተወግዘው የተለዩ ሲሆን ምስጢራትንም የመፈጸምና ጳጳሳትንም የመሾም መብታቸውንም ተነጥቀዋል፡፡

- ባለንበት ዘመን ይኸ ሐዋርያዊ ውርስ ተጠብቆ የሚገኝባቸው ጥቂት አብያተ ክርስቲያናት ይገኛሉ፡፡ እነዚህም ኦርቶዶክሳውያን አብያተ ክርስቲያናት ናቸው፡፡ ዘመናውያኑ የ#ክርስቲያኖች የሃይማኖት ቡድኖች; የሐዋርያዊ ትውፊትን ወይም ቅብብልን አስፈላጊነት በአቋም ይቃወማሉ፡፡ ይኸም ማለት የመጀመሪያውን መቶ ክፍለ ዘመን ቤተክርስቲያን ይቃወማሉ ማለት ሲሆን - በመሆኑም እነዚህም እውነት የሌለባቸው ይባላሉ፡፡

- ክርስቲያኖች የእግዚአብሔርን ስጦታ በ#ጸሎታቸውና በስብሰባዎቻቸው; መናፍቃን ከሚፈጽሙት ጊዜያዊ ደስታ ካለበት ጎጂ #መንፈሳዊነት; መለየት ይጠበቅብናል፡፡

# እውነተኛኝኙቱ ቤ/ክ በየት ትገኛለች?
# እንዴትስ ትታወቃለች?...

- እውነተኛ ስጦታና በረከት የሚገኘው ከነፍስ ሰላም፤ ለእግዚአብሔርና ለባልንጀራችን ካለን ፍቅር፤ ከርኅራኄ፤ ከደግነት፤ ከትዕግሥት፤ ከበጎነትና ቅዱስ ጳውሎስ ለገላትያ ሰዎች በጻፈው መልእክቱ ከጠቀሳቸው ሌሎች መንፈሳዊ ፍሬያት ነው። ገላትያ 5:22-26

- ሌላው እውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን የምትታወቅበት ምልክቷ መከራዋ ነው። ሰዎች እውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን የትኛይቱ እንደሆነች ለማወቅ ቢቸገሩ እንኳ ዲያቢሎስና ጠላቶቿ ግን ጠንቅቀው ያውቋታል። እነዚህ ዘወትር ቤተክርስቲያንን ይፈታተኗታል ሊያጠፏትም ይጣጣራሉ።

- ከቤተክርስቲያን ታሪክ ጋር ራሳችንን ብናስተዋውቅ ለእምነታቸው በተሰው ሰማዕታት ልጆቿ በእምባና በደም የተጻፈ እውነትን በውስጧ እናገኛለን።

- ይኽ መከራ በመጀመሪያ በሊቃነ ካህናት፤ በጸፎችና በፈሪሳውያን አማካይነት በዘመነ ሐዋርያት በሐዋርያት ላይ ተፈጽሟል። የሐ. ሥራ 7 : 1 — 62

- በመቀጠልም በሮማውያን ቄሳሮች ለሦስት መቶ ዘመናት የተፈጸመው የቤተክርስቲያን የስደትና የመከራ ዘመን ተተክቷል።

# <u>እውነተኛኘኙቱ ቤ/ክ በየት ትገኛለች? እንዴትስ ትታወቃለች?...</u>

- ከሮማውያኑም በማስከተል በቤተክርስቲያን ላይ የዐረብ ሙስሊሞች ሰይፍ አርፎባታል፡፡

- በመቀጠልም ኢአማንያንና መናፍቃንም ከመቼውም ጊዜ በበለጠ ሁኔታ በርካታ ክርስቲያኖችን ፈጅተዋል፤ መጻሕፍትንና አብያተ ክርስቲያናትንም አቃጥለዋል፡፡ ይሁን እንጂ ጌታችንም #የገሃነም ደጆችም አይችሉአትም፡፡; ማቴ 16፡18፡፡ ብሎ ቃል እንደ ገባላት የሰማዕታቱ ደም አዳዲስ አማንያን ክርስቲያኖችን ለማብቀል የተዘራ ዘር እየሆነ እንደ ተአምር ታይቷል ሲታይም ይኖራል፡፡

- የእግዚአብሔርን ቤተክርስቲያን ከሐሰተኛ ትምህርት የምንለይበት የመጨረሻው መንገድ ትክክለኛ የሆነ ንጽጽር ነው፡፡ እውነተኛይቱ ቤተክርስቲያን ከዘመነ ሐዋርያት ጀምሮ የግድ መኖር አለባት፡፡ ሁሉም #ክርስትና; መሰል ሂደቶች እንዴት እንደተፈጠሩና እንደተስፋፉ ማስረዳት ተገቢ አይመስለንም፡፡ ይሁን እንጂ በ16ኛው ወይም እንደዚህ ባሉ መቶ ክፍለ ዘመኖች የተፈጠሩ በዘመነ ሐዋርያት ያልነበሩ #አብያተ ክርስቲያናት; ቢገጥሙን በዘመነ ሐዋርያት የማይታወቁና እውነተኛዋንም ቤተክርስቲያን አለመሆናቸውን መግለጽ ግን ከበቂ በላይ ነው፡፡

# እውነተኛኘኘቱ ቤ/ክ በየት ትገኛለች?
# እንዴትስ ትታወቃለች?...

- አንዳንድ ቡድኖች መሰረታቸውን በሉተር፤ በተከታዮቹ ወይም ሌሎች ቡድኖች ላይ አድርገው ራሳቸውን የክርስቶስ ቤተክርስቲያን አድርገው ሲያቀርቡ ተቃውሞን መግለጽ ተገቢ ነው፡፡ እነዚህም ቡድኖች፡- #ሉተራውያንን፤ ካልቪኒስቶችን፤ ፕሪስባይቴሪያንስን፤ ቀጥሎም ባፕቲስቶችን፤ አድቬንቲስትን፤ ሞርሞንስን፤ የይሆዋ ምስክሮችን፤ ጰንጤዎችን... እነርሱን የሚመስሉ ሌሎችንም; የሚያካትቱ ናቸው፡፡ እነዚህ ቡድኖች በጌታችን ወይም በሐዋርያቱ የተመሰረቱ አይደሉም፡፡ ነገር ግን እንደ #ሉተር፤ ካልቪን፤ ጆሴፍ ስሚዝ፤ ሜሪ ቤከር ኤዲ፤ ቻርለስ ራስልን በመሳሰሉ ሌሎች የኋለኛ ዘመን ነቢያት; የተመሰረቱ ናቸው፡፡

- የዚህ ትምህርት ዋና ዓላማ የቤ/ክንን እምነት፤ ትምህርትና ታሪካዊ ሂደት ለኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤ/ክ ምዕመናን ማስገንዘብና #በኋለኛ ዘመን ነቢያት-መናፍቃን; የተመሰረቱ ቡድኖችና ትምህርታቸው በጌታችን ከተመሰረተችው አንዷቱ ቅድስት ቤተክርስቲያን እንዴት እንደሚለይ ማስረዳት ነው፡፡

- ሁሉንም ባንመለከትም አሁን ክርስቲያኖች ነን ብለው ከሚጠይቁ #ሃይማኖቶች; መካከል እንዳንዶቹን እንመለከታለን፡፡ ይሁን እንጂ አስቀድመን የምንመለከተው እውነተኛይቱን፤ ቅድስቲቱንና ሐዋርያዊቷን ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን ነው፡፡

ይቀጥላል

… ኦርቶዶክሳዊት ተዋሕዶ ቤተክርስቲያን

ወስብሐት ለእግዚአብሔር።